# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

## የዕለቱ ምስባክ

አርውዮ ለትለሚሃ
ወአስምሮ ለማእረራ
ወበነጠብጣብከ ትበቊል ተፈሢሃ

ትልምዋን ታረካለህ
ቦይዋንም ታስተካክላለህ
በነጠብጣብ ታለሰልሳታለህ

መዝ ፷፬፥፲

ወንጌል፥ ማቴ ፲፫፥፩-፴፩
ቅዳሴ፥ የጌታችን ቅዳሴ (ዘእግዚእነ ነአኵተከ)

## የዕለቱ ትምህርት

### ዋጋችን እንደ ፍሬአችን ነው።

(ዕብ ፮፥፯-፰)

የዕለቱን ትምህርት የወንጌሉን ማብራሪያ ካለፈው ሳምንት እሑድ ይመልከቱ፤ ተጨማሪው ትምህርት እነሆ።

በቅዳሴ ጊዜ በአንደኛው ዲያቆን የተነበበው መልእክተ ጳውሎስ በክረምት ለሚዘራባት ገበሬ በጐ ፍሬን የሚሰጥ እህል ታበቅል ዘንድ እግዚአብሔር የበረከት ዝናም በመስጠት የመሬትን ትልምዋን ያረካላታል፤ ቦይዋን ያስተካክልላታል፤ በነጠብጣብም ያለሰልሳታል (መዝ ፷፬፥፲)። ታዲያ ዘወትር በእርስዋ ላይ የሚወርደውን ዝናም የምትጠጣ ለሚያርሷትም ፍሬ የምትሰጥ መሬት ከእግዚአብሔር በረከት ትቀበላለች። ነገር ግን እሾህና አሜከላ የምታበቅል መሬት ዋጋ ቢስ ትሆናለች፥ ለመርገም የቀረበች በመጨሻ ሰዓት ትቃጠላለች (ዕብ ፮፥፯-፱) በማለት ከያዝነው የክረምትና የዘር ወቅት ጋር በማያያዝ በማስጠንቀቂያ ትምህርት ይሰጣል። ገበሬው መላልሶ ያረሳት እግዚአብሔርም በዝናም ያረሰረሳት መሬት በጐ ማፍራት እንደሚጠበቅባት አንድ ጊዜ የክርስቶስ ብርሃን የበራላቸው፤ ሰማያዊውን ስጦታ የቀመሱ በመንፈስ ቅዱስ የተባረኩ፣ መልካሙን የእግዚአብሔር ቃልና የሚመጣውን ዓለም ኃይል የቀመሱ ሰዎች በክርስቶስ ፍቅር ሊኖሩ ይገባቸዋል። በአንጻሩ መሬትዋ እሾህ አሜከላ ብታፈራ የተዘራባትን በጐ ዘር ብትቆረጥም፣ የዚያች እርሻ መጨረሻ በእሳት መተኮስና መቃጠል እንደሚሆን ክርስቲያኖችም የእግዚአብሔርን ጸጋ ረግጠው የተሰፋውን ቃል ጥለው ለኃጢአት መኖር ከጀመሩ እነርሱን መልሶ በንስሐ መለወጥ ከባድ ይሆናል። በግብራቸው የእግዚአብሔርን ልጅ መልሰው ይሰቅሉታል። በመሆኑም የመጨረሻ እድላቸው እሾሃማዎች ስለሆኑ መቃጠል ይሆናል።

ወድ አንባቢ ሆይ፥ ቅዱስ ጴጥሮስ ከሃይማኖት ወደ ክህደት የምትሄድን ነፍስ በማስመልከት «በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እውቀት ከዓለም እርኩሰት ካመለጡ በኋላ

### የክረምት ሁለተኛ ሰንበት

ከሰኔ ፳፭ እስከ ሐምሌ ፲፭ ቀን ድረስ በዐተ ክረምት (የክረምት መግባት) ይባላል። ሥርዓተ አምልኮውም የተመሰረተው ወቅቶችን ስለሚለውጠው አምላክ ኃይል፣ ስለ ደመናዎች፣ ስለ ዘር፣ እግዚአብሔር በጋውን አሳልፎ ክረምቱን ስለማምጣቱ፣ ደረቁን ስለማለምለሙ በሚያስታውሱ ክፍላተ መጽሐፍት ላይና መዝሙራት ላይ ነው። በተጨማሪም በክረምት ነገረ ትንሣኤ ይሰበካል፤ የዘሩ መዘራት እንደ መሞት መቀበር፤ መብቀሉ ደግሞ እንደ መነሳት ይወሰዳል። በምሳሌ ይሰበካል ክረምት ቢዘገይም እንደማይቀር ምጽአትም ሞትም እይቀሩምና በንጽጽር ይሰበካል።

### የዕለቱ የቅዱስ ያሬድ መዝሙር ርዕስ

ይሰጥዎ ወይሰማዖ ጸሎቶ ለኵሉ ለዘሰአሎ
«ለለመነው ሁሉ ጸሎቱን ይሰማለታል ይመልስለታልም»

### በቅዳሴ ሰዓት የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች

| | ንባብ | አንባቢ |
|---|---|---|
| 1 | ዕብ ፮፥፯-ፍጻሜ | ዲያቆን (ገባሬ ሰናዩ) |
| 2 | ፩ኛ ጴጥ ፫፥፰-፲፭ | ዲያቆን (ንፍቅ ዲ.) |
| 3 | የሐዋ ሥራ ፲፬፥፰-፲፱ | ረዳቱ ቄስ (ንፍቅ ካህን) |

ዳግመኛ በእርስዋ ተጠልፈው የተሸነፉ ቢሆኑ ከፊተኛው ኖሯቸው ይልቅ የኋለኛው የባሰ ሆኖባቸዋል» አለ (፪ኛ ጴጥ ፪፥፳)። በመሆኑም መልካም ሕይወት ላይ የሚበቅለውን እሾህ ካላጠፋን እሾህ የእሳት መነሻ ምክንያት እንደሆነ (ዘጸ ፳፪፥፮ ። ኢሳ ፲፥፲፯) በሕይወታችን ላይ የፍርድ እሳት ያቀጣጥላል። እሾህ የክፉ ሰዎች ምሳሌ ስለሆነ (ዘኍ ፴፫፥፶፭ ። ናሆም ፩፥፲) ክፋታችን ለፍርድ አሳልፎ ይሰጠናል። እሾህ የሰውን ድካም ከንቱ የሚያደርግ የሥራ እንቅፋት እንደሆነ (ዘፍ ፫፥፲፰ ። ምሳ ፳፬፥፴፩ ። ኤር ፲፪፥፲፫ ። ማቴ ፲፫፥፯) ሕይወታችን መከራ የበዛበት ይሆናል። በመሆኑም በፈጣሪ ፊት የመርገም ምሳሌ በሆነው እሾሃዊ ሕይወት እንዳንገኝ ከክፋታችን እንመለስ የሚል ነው፤ ቃሉ በውስጣችን ይሥራ፤ ጫካው ልባችን ይመንጠር ወንጌል ይብቀልበት፤ እሾሃማው ሕይወታችን ይውደቅ፤ ምድረ በዳው ልባችን ይረስርስ በጐም ነገር ይብቀልበት። በመርገም ፋንታ በረከት፤ በሞት ፋንታ ሕይወት፤ በፍርድ ፋንታ ምሕረት እንዲበዛልን ዘወትር ስሙ የሚጠራለት ቃሉን የሚሰማው ሕይወታችን ለበጐ ነገር ይቅና። እሾሃማና ጠማማ የሆነው የግራር ዛፍ ልቦናችንን በሙሉ መንጥሮና ጠርቦ፣ አቅንቶና አስተካክሎ ታቦቱ ያደረገው ጌታ፣ በጫካው ልቦናችን ቃሉን አዝንሞ ቁም ነገርን፣ ፍቅርን፣ ሰላምን ያመረተው በሕይወታችን በጐ ነገርን ይዘራ ዘንድ መልካም ዘር ይዞ የወጣው የሕይወታችን ጌታ ክርስቶስ ምስጋና ይግባው አሜን።

ጥቅስ በግእዝ፥
ዘኒ ይዘርእ እንዘ ይሴፎ ኪያከ፤ ወዘኍ የአርር ብእለ ጸጋከ ከመታወርድ ዝናመ በቃለ ትእዛዝከ እግዚአ ለሰንበት ስብሐት ለከ

የሚዘራውም አንተን ተስፋ አድርጐ ይዘራል፤ የጸጋህን ሃብት መከር የሚሰበስበውም አንተን ተስፋ ያደርጋል። ያውም በቃልህ ትእዛዝ ዝናምን ታወርድ ዘንድ ነው፤ የሰንበት ጌታ ሆይ ምስጋና ይገባሃል። (ቅዱስ ያሬድ)

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ... አሜን።

ከመምህር ልዑለ ቃል አካሉ ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ፩ኛ መጽሐፍ የተወሰደ
EthiOrthodox e-mail Outreach EthiOrthodox@AOL.COM